የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ

AFAR REGION NEGARIT GAZETA

OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

አስራ አንደኛ ዓመት ቁጥር 58 ሠመራ ህዳር-----ቀን 2003 ዓ.ም.	በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት	11h year No.58 samara --- November...../2011

ማውጫ

የአደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ፕሮገራም ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤትን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ..... ገጽ 1

አዋጅ ቁጥር 58/2 00 3 ዓ.ም

የአደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ፕሮገራም ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤትን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

መግቢያ፣

በክልሉ በተደጋጋሚ በሚከሰት የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች የክልሉ ህዝብ ለተደጋጋሚ ድርቅና የምግብ ዕጥረት መጋለጡ&በዚህም በክልሉ የምግብ ዋስትናን በዘላቂነት ለማረጋገጥ የክልሉ መንግስት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠቱ&

በዚህም የምግብ ዋስትናውን በአስተማማኝ ሁኔታ በማረጋገጥ የክልልን ህዝብ ከዕርዳታ እህል ጥገኝነት ለማላቀቅ የሚያስችል'የተደራጀና የተቀናጀ የማስተባበር ስራ የሚሰራ ራሱን የቻለ ተቋም ማቋቋም በማስፈለጉ &

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ም/ቤት በተሻሻለው የክልሉ ህግ መንግስት አንቀጽ 47/3//ሀ/ በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌ

1. አጭር ርዕስ፣

ይህ አዋጅ #የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ፕሮገራም ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት መቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ---/2 00 3 ዓ.ም;. ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

ክፍል ሁለት

ስለክልሉ የአደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ፕሮገራም ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት መቋቋም'ዓላማ'አደረጃጀትና ስልጣንና ተግባር

2. መቋቋም

1. የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ፕሮገራም ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት /ከዚህ በኋላ #ጽህፈት ቤት; ተብሎ የሚጠራ/ ራሱን የቻለ ህጋዊ ሰውነት ያለው የክልሉ መንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
2. የጽህፈት ቤቱ ተጠሪነት ለክልሉ አርብቶ አደርና ግብርና ልማት ቢሮ ይሆናል።

3. ዓላማ

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ፕሮገራም ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ዓላማ'የክልሉ ህዝብ በዘላቂነት ከሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋ ስጋት ነጻ የሆነ ኑሮ እንዲኖር ከማስቻል ባሻገር የምግብ ዋስትናውን በዘላቂነት እንዲያረጋግጥ ማስቻል ነው።

4. ዋና መስሪያ ቤት

የጽህፈት ቤቱ ዋና መስሪያ ቤት በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዋና ከተማ በሰመራ ይሆናል።

5. የጽህፈት ቤቱ ስልጣንና ተግባር

1. ጽህፈት ቤቱ በህግ የተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስፈልገውን ሥልጣን ሁሉ ይኖረዋል።
1. ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1/ በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ምክንያት የሚደርስ አደጋ ለመከላከል የሚያስችሉ ፖሊሲዎችንና ስልቶችን ያቅዳል&ሲፈቀድም አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በስራ ላይ ያውላል፣

2/ አግባብ ካላቸው የመንግስት አካላት ጋር በመተባበር አደጋ ለመከላከል የተቀየሱ ፖሊሲዎችንና ስልቶችን በስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል&

3/ ከክልል መንግስት በሚሰጥ መመሪያ መሰረት ከአገር ውስጥ ማንኛውንም ዓይነት ዕርዳታ ይጠይቃል& የዕርዳታ ግኝትና አስተዳደርን በሚመለከት በፌደራልና በክልል መንግስት በሚወጡ መመሪያዎች መሰረት ከዕርዳታ ሰጪ አካላት ጋር ግንኙነት ይፈጥራል'

4/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አደጋ ሊመጣ የሚችልበትን ምክንያት አስቀድሞ ያጠናል&ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል'አደጋው እንዳይደርስ ጊዜያዊና ዘላቂ የመከላከል እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል'

5/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አደጋ በሚደርስበት ጊዜ የአደጋው አይነት መጠንና ስፋት እያጠና ሊወሰድ የሚገባውን ዕርምጃ ጭምር ለክልሉ መንግስት ያሳውቃል&ዕርዳታ የሚደረግበትን ቅደም ተከተል ይወስናል'

6/ ማንኛውመ አይነት ዕርዳታ ለተረጂው በወቅቱ እንዲደርስ ያደርጋል&

7/ የዕርዳታ ፕሮግራሞች ማስፈጸሚያ የሚያስፈልጉ ልማት ነክ ፕሮጀክቶችን ዝግጅትና አፈጻጸም ያስተባብራል&

8/ በክልል መንግስት እንዲሰሩ የሚያስችል ፈቃድ ያላቸውን መንግስታዊ ያልሆኑ የግል ዕርዳታ ሰጭ ድርጅቶችን ስራ ያስተባብራል&

9/ በክልል ረጅም&መካከለኛና አጭር ጊዜ ዕቅድ ውስጥ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚካሄዱ ስራዎች እንዲካተቱ ያደርጋል'ሲፈቀደም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል'

10/ ምግብ ዋስትናን የሚመለከቱ ጥናቶችን ያካሂዳል'

11/ በምግብ አጠር አካባቢዎች የህብረተሰቡ የምግብ ዋስትና ሁኔታ ለማሻሻል እንዲቻል የተለያዩ የገቢ ማስገኛ ስራ ዕድሎችን ለመፍጠር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞቹ እንዲጠኑ ያደርጋል& ሲፈቀድም ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል'

12/ በምግብ ዋስትና በኩል የሚካሄዱ የተለያዩ የልማት ስራዎችን ያስተባብራል&

13/ ለተቀናጀ የምግብ ዋስትና ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች ማስፈጸሚያ የሚውል ፈንድ ከመንግስትና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ከህብረተሰቡ እንዲገኙ ያስተባብራል &

14/ የሴፍቲ ኔት ፕሮግራሞችን በበላይነት ይመራል&

15/ ዓላማውን ለማስፈጸም ከተለያዩ አካላት ጋር ግንኙነት ይፈጥራል &

16/ ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት ያደርጋል&

6. <u>አቋም ፣</u>

1. ጽህፈት ቤቱ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉትን አካላት ይኖሩታል&

ሀ/ አንደ የጽህፈት ቤት ኃላፊ' እና

ለ/ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ሠራተኞች

2. የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ በክልሉ ርዕስ መስተዳድር ይሾማል ።

3. የኃላፊው ተጠሪነት ለክልሉ አርብቶ አደርና ግብርና ልማት ቢሮ ኃላፊ ይሆናል።

7. <u>የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ ስልጣንና ተግባር፣</u>

1.የጽህፈት ቤቱ ዋና ስራ አስፈጻሚ በመሆን የጽህፈት ቤቱን ስራዎች ይመራል& ያስተዳድራል::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከተው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ኃላፊው&

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ላይ ለጽህፈት ቤቱ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል።

ለ/ በክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ህግ መሰረት የጽህፈት ቤቱን ሠራተኞች ይቀጥራል& ያስተዳድራል ያሰናብታል።

ሐ/ የጽህፈት ቤቱን አመታዊ በጀትና የሥራ ኘሮግራም ያዘጋጃል& ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል።

መ/ ለጽህፈት ቤቱ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ኘሮግራም መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል።

ሠ/ ጽህፈት ቤቱን በሶስተኛ ወገኖች ዘንድ ይወክላል።

ረ/ የጽህፈት ቤቱን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለመንግስት ሪፖርት ያቀርባል።

<u>ክፍል ሶስት</u>

<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

8. በጀት

የክልሉ መንግስት የጽህፈት ቤቱን በጀት ይመድባል'።

9. የሂሳብና መዛግብት አያያዝ

1. ጽህፈት ቤቱን የተሟላና አግባብነት ያላቸው የሂሳብ መዛግብትን ይይዛል።

2. የጽህፈት ቤቱ የሂሳብ መዛግብትና ሌሎች ገንዘብ ነክ ሰነዶች በየአመቱ በክልሉ ዋና ኦዲተር መ/ቤት ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር ይመረመራል።

10. ስለመብቶችና ግዴታዎች መተላለፍ

በአዋጅ ቁጥር **<u>30/98</u>** ተቋቁሞ ለነበረው የአደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ቢሮ ተሰጥቶ የነበረው መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለጽህፈት ቤቱ ተላልፈዋል።

11. ደንብ የማውጣት ስልጣን

በዚህ አዋጅ መሰረት የክ MK< Se}ዳድር U ክ` u?ት ይህን አዋጅ KTe ፈጸ U የ T>ያ e ች M ደንብ K=ያወጣ ይች LM::

12. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ ምክር ቤት ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሠመራ ---------- 2 በ0 3 ዓ.ም.

እስማኤል ዓሊሴሮ
አፋር ብ/ክ/መንግስት
ርዕስ መስተዳድር